# ኦርቶዶክሳዊ መዝሙራት



## በደብረ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት መዝሙር ክፍል የተዘጋጀ

ልዩ ጥራዝ 1
የሠርግ መዝሙር ጥራዝ
25/5/2011 ዓ.ም

ለመልካም ጋብቻ ሆነዋል አርአያ
ተክለሃይማኖትን ጻድቁን ያፈሩት
ቀን ከሌሊት ተግተው ነው በጾምና
ጸሎት
ኑ ተመልከቱልኝ የአማኑኤልን ሥራ
ኑ ተመልከቱልኝ የእመቤቱን ሥራ
በሠርጉ ተገኝቶ ከአማኑኤል ጋር
/ከመላእክት/ ጋር

72. ንጽህት ድንግል
ንጽህት ድንግል ቡርክት
የአምላክ እናት እመቤት
ልጆችሽ ሙሽሮች ሁለቱም አንድ ሆኑ
ተዋሃዱ ተጣመሩ በቅዱስ ቁርባኑ
ፍጹም መንፈሳዊ ልዩ ፍቅር
አንቺ ያለሽበት መልካም ትዳር
መሠረቱ ዛሬ ልጆችሽ
ቅድስት ሆይ ባርኪያቸው
ተገኝተሽ
ድንግል ጉጂቸውን ቀድሰሽ
እውነተኛ ፍቅር መሥርተሽ
በመካከላቸው ተገኝተሽ
ሁሉን አሰጪያቸው አግልደሽ
ሙሽሮቹም አምነው በምልጃሽ
እናታችን ባርኪን ነይ ሲሉሽ
ፈጥነሽ ድረሽና በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሽ መሃላቸው
አንቺን ለሚወዱሽ ለሚያምኑሽ
የሕይወት አጣፋጭ ቅመምነሽ
ሙሽሮቹም ዛሬ ይጠሩሻል
የጉጂችን ፋና ነይ ይሉሻል
ቃና ዘገሊላ ተገኝተሽ
መልካሙን ጋብቻ የባረክሽ
ዛሬም ከልጆሽ ጋር በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሽ መሃላቸው

73. ሙሽራው
ሙሽራው /4/ እጹብ ነው ደስታው
ሙሽራው /2/
ሙሽራዋ /4/
እጹብ ነው ደስታዋ
ሙሽራዋ /2/
እንደ አደይ አበባ ሙሽሮች መልካቸው
በለምለም መስክ ያለፍሬ መሰላቸው
ልክ እንደ ጨረቃ እንደ ሰማይ ፀሐይ
መልካሙ ስራቸው በራ በአደባባይ
ካባዋን ደርባ በጥበቧ ላይ
የተዋህዶ ልጅ ደምቃ ስትታይ
በቤተክርስቲያን ሥርዓት በማደጓ

ይኸው መሰከረ የሙሽሪት ሠርጓ
መልካም ሥነ ምግባር ፍቅር የከበበህ
የእመ ብርሃን ልጅ አቤት ማማርህ
ከመቼሙም ይበልጥ ዛሬ ተውበሃል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያህን ከቦሃል
የእመቤቴ ጸዳል ዙሪያህን ከቦሃል
መልካም ሥነምግባር ፍቅር
የከበበሽ
የእመብርሃን ልጅ አቤት ማማርሽ
ከመቼውም በላይ ዛሬ ተውበሻል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያሽን
ከቦሻል
የእመቤቴ ጸዳል ዙሪያሽን ከቦሻል

74. በተዋህዶ ምስጢር ስናይ
እሰይ እሰይ እሰይ /2/
በተዋህዶ ምስጢር ስናይ
እሰይ እሰይ በአዳም ተጀምሮ
" " የአንድ አካል ምስጢር
" " በገነት ሲኖሩ
" " በጽድቅ ምድር
አካሌ ናት አላት ሔዋንን በፍቅር
እሰይ እሰይ መካን ሆነው ሳሉ
" " ሐናና ኢያቄም
" " የፀናው አንድነት
" " አልተነጣጠለም
" " በእምነት ቢቆሙ
" " በጾም በጸሎት
ድንግል ተወለደች ልትሆን መድኃኒት
እሰይ እሰይ ዛሬም በሙሽሮች
" " ይኸንን አይተናል
" " በቅዱስ ጋብቻ
" " በማይነጣጠል
ምሥጢር ተፈፀመ በሥርዓት ተክሊል
እሰይ እሰይ የተዋህዶ ምስጢር
" " እጅግ የጠለቀ
" " በእምነት ልቦና
" " ፈፅሞ ታወቀ
ዛሬም በሙሽሮች ክብር ተደነቀ

75. የሀብከ ዮም
የሀብከ ዮም የሀብከ መድኃኒዓለም
እድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም /2/
ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኒዓለም
እድሜ የማቱሳላ የአብርሃም/2/
አደራ ሙሽራዉ አደራ በማርያም ድንግል /2/
እንዳትረሳ ቤተክርስቲያን /2/
እንዳሳደገችህ /2/ በቃል ወንወጌል /2/
ይኸዉ አበቃችህ ደግሞ ለተክሊል/ለቁርባን/ /2/

አደራ ሙሽሪት አደራ በማርያም
ድንግል/2/
እንዳትረሳሽ ቤተክርስቲያን /2/
እንዳሳደገችሽ /2/ በቃለ ወንወጌል /2/
ይኸዉ አበቃችሽ ደግሞ ለተክሊል/ለቁርባን/
/2/

76. የሀብክ ዮም
የሀብክ ዮም የሀብክ መድኃኒዓለም
እድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም /2/
ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኒዓለም
እድሜ የማቱሳላ የአብርሃም/2/
በቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች የተወሰናችሁ
ክርስቶስ ተገኝቷል በመካከላችሁ/2/
የድንጋዮቹን ጋን ወይኑን/2/ ሊሞላበት
ከድንግል ማርያም ጋር ተገንቷል በዚህ ቤት /2/
ደስታዉን አይቶ አምላክ ፍጹም ተደስቷል
ሊባርካችሁ እጆቹን ዘርግቷል /2/
በሕይወታችሁም ፍቅር /2/ ቅመም ሆኖ
ትኅትናን ይስጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ/2/
ሠርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር የሞላበት
በሕይወታችሁ ዉስጥ ክርስቶስ ይግባበት
በሕይወታችሁ ዉስጥ አምላክ ይኑርበት/2/
የበረከት ፍሬ ጸጋዉ እንዲበዛላችሁ
ዛሬ ተደስቱ አምላክን ይዛችሁ
ዛሬ ተደስቱ ድንግልን ይዛችሁ
ከሥጋ ወደሙ እግዚአብሔር ስለመረተጣችሁ
የመንፈስ ቅዱስ ሕፃናቶች ናችሁ /2/

77. አምሮ ሲያበራ
አምሮ ሲያበራ ኑ ተመልከቱ /2/
በእግዚአብሔር ክብር ሲመላ ቤቱ /2/
ማነው የገባው በዚህ ጣራ ስር
ለሙሽሮቹ ደስታ ሊያበሥር
ቤቱ ተሞላ ሰላም ፍሰሐ
እናቅርብለት ምስጋና እምሃ
በአብርሃም ቤት የተገለጠው
በአልዓዛር ቤት እራት የበላው
ከእናቱ ጋር ገባ ከቤቱ
ቤተዘመዱ ኑ ተደሰቱ
የእኛ ሙሽራ ደስ ይበልህ
ታላቅ እንግዳ ገብቷል ከቤትህ
ሙሽራችን ሆይ ደስ ይበልሽ
የሰማይ ንግስት ጐበኘችሽ
ለእድምተኞች መልካም ወይን አለን
የቃናው ጌታ የጠመቀልን
እናፍርም እኛ እንግዳ ጠርተን
አምላክ ከእኛ ጋር ስለሆነልን

78. ንሴብሖ ለሥላሴ
ንሴብሖ ለሥላሴ /2/
ክብር ተመስገን አምላክ ሙሴ /2/
የእኛ አማላጅ እናታችን
ነይ ነይ ወደ እኛ እመቤታችን
ፈጥነሽ ተገኚ በመሃላችን
ና ወደእኛ ሚካኤል /2/
መልአክ ምክሩ ለልዑል
ከእግራችን ይውደቅ ሳጥናኤል
ና ወደእኛ ገብርኤል /2/
ከእሳቱ አውጣን ከነበልባል
በክንፍህ ጥላ እንጠለል
ና ወደእኛ ዑራኤል /2/
እንደ ቅዱስ ዕዝራ ሱቱኤል
ጥበብን ስጠን ማስተዋል
ና ወደእኛ በፈረስ
የልዳው ፀሐይ ጊዮርጊስ
ገድልህን ሰምተን እንፈወስ
ና ወደእኛ ተክለሃይማኖት /2/
ይጠብቀን የአንተ ጸሎት
ጸንተን እንድንቆም በሃይማኖት /2/

79. ሙሽራው ደስ ይበልህ
ሙሽራው ደስ ይበልህ /2/
ፍቃዱ ሆኖ ጌታህ
ዕፁብ በረከት ሰጠህ
ሙሽሪት ደስ ይበልሽ /2/
ፍቃዱ ሆኖ ጌታሽ
ዕፁብ በረከት ሰጠሽ
ሁለት አይደለም ቃላቸው
ዘወትር አንድ ነው ድምፃቸው
የኑሮን ሕይወት እንዲገፉ
በአንድነት ሆነው ተሰለፉ
ምድራዊ አይደለም ሰማያዊ
የማይመረመር ምስጢራዊ
በሥጋ ወደሙ አንድ ሆነው
ሙሽሪትና ሙሽራው
ሁለት አይደለም ኑሮአቸው
ከእንግዲህ አንድ ነው ኅጆአቸው
መሠረት ጣራ ግድግዳው
እግዚአብሔር ነው ምሰሶው

80. አዳም ሆይ
አዳም ሆይ እህት አገኘህ /2/
በሐሴት ይሙላ ልቡናህ ደስ ይበልህ
ሔዋን ሆይ ወንድም አገኘሽ /2/
በሐሴት ይሙላ ልቦናሽ ደስ ይበልሽ
ብቻህን መሆንህን እግዚአብሔር አይቶ
የከበደ እንቅልፍን አንተ ላይ አምጥቶ

አጥንት ወሰደና አንዷን ከጎንህ
እህት እንድትሆንህ ሔዋንን ሰጠህ
ሐዋን ሆይ ...
አዳም ሆይ ...
ከጎኑ ተፈጥረሽ በሥላሴ ጥበብ
አክብሪው ባልሽን ተዋደዱ ከልብ
አዳም ከጎንሽ ነው የሚያስብልሽ
የአምላክን ስጦታ ውሰጅው ፈቅደሽ
አዳም ሆይ ...
ሔዋን ሆይ ...
አካልህ ሔዋን ናት ያንተ ዕጣ ፈንታ
አምላክ ባረካችሁ በብዙ ደስታ
የኑሮን ተካፋይ አምላክ ከሰጥህ
ሕይወቱ ነሽ ብለህ ሂድ ወደ ሚስትህ
ሔዋን ሆይ ...
አዳም ሆይ ...

81. ቤታችን ይቀደስ

ቤታችን ይቀደስ በረከት ይሙላ /2/
ፍቅር አንድነት አድለን ጌታ /2/
ቤታችን ይቀደስ የማያልቅበት
" " ለጋስ አምላክ ነህ
" " ገበናችንን
" " የምትሰውረው
" " የጐጆአችን ውስጥ
" " ሁሌ የምትኖረው
ቤታችን ይቀደስ ለጾም ለጸሎት
" " እንድንተጋ
" " ለሠናይ ምግባር
" " እንድንነሣ
" " ዘወትር ጠዋት ማታ
" " እንድናስብህ
" " በትዳራችን
" " ከኛ አትለየን
ቤታችን ይቀደስ የምናመልከው
" " አንተን ብቻ ነው
" " ተስፋችን ባንተ
" " እጅግ ፅኑ ነው
" " ማን ይመስልሃል
" " በምድር በሰማይ
" " ወረት የሌለህ
" " ቅዱስ አምላክ ነህ

82. መጥተዋል ጌታ

መጥተዋል ጌታ ወደ አንተ /2/
ሙሽሮቹ ጌታ ወደ አንተ /2/
የቅዱሳን ክብር የእኛ ተስፋችን
የማትፀየፈን በኃጢአት
ብንወድቅም
ለጐረቤታችን ምሣሌ እንድንሆን
መዋረድ መፋቀር ሰላሙን አድለን
መጥተዋል ጌታ ወደ አንተ /4/
ሙሽሮቹ ጌታ ወደ አንተ /2/
ሁሉን እንድንችል ኃይሉን
የምትሰጠን
መፅናኛ ደጋፊ አባት የምትሆነን
ብናጣም ብናገኝ አንተ አለኝታችን
ነህ
እንዳንደክም እንዳንዝል ፅናት
የምትሆነን
መጥተዋል ድንግል ወደ አንቺ /4/
ሙሽሮቹ ድንግል ወደ አንቺ /2/
ቃና ዘገሊላ በዛ በሠርግ ቤት
አማላጅነትሽ በተገለፀበት
ለልጅሽ ነግረሽው ጋኑን
ያስሞላሽው
ዛሬም ለሚጠሩሽ ለሚማፀኑሽ
ፈጥነሽ ድረሽና ባርኪው ጎጆሽን
መጥተዋል ድንግል ወደ አንቺ /4/
ሙሽሮቹ ድንግል ወደአንቺ /2/
ወላዲተ አምላክ ቅድስተ ቅዱሳን
በጭንቀት ደራሽ ነሽ ሩህሩህ
እናታችን
ወደ አንቺ ስንመጣ ወደ ደጃፍሽ
እቅፍ ድግፍ አድርጊን
እንዳንጠፋብሽ

83. ጌታ ሆይ እባክህ

ጌታ ሆይ እባክህ እንለምንሃለን /2/
በፍቅር በደስታ እንድንኖር እርገን /2/
ጌታ ሆይ እባክህ በኃጢአት
ብንወድቅም
" " " ምንም ብንበድልህ
" " " መአትህ የራቀ
" " " ብዙ ነው ምሕረትህ
" " " አንተ ሃብታችን ነህ
" " " የራስ ዘውዳችን
" " " ውስጣችን የምትኖር
" " " የማትለየን
ጌታ ሆይ እባክህ አንተ ካልባረከው
" " " ትዳር ጎጆውን
" " " በከንቱ መድከም ነው
" " " መልፋት መባዘን
" " " በቅዱስ ፍቃድህ
" " " ሁሉን ትሠራለህ
" " " የጀመርከውን ቤት
" " " ታከናውናለህ
ጌታ ሆይ እባክህ እንድትሰጠን ለእኛ

ወደ አዲሱ ቤቱ ለሙሽራው
መግባቱን አይታችሁ
እስቲ ዘምሩላት ለሙሽሪት
በአንድነት ሆናችሁ
ረዳት አገኘች የእኛ ሙሽራ
ጥሩ ወንድምን
ሥነ ምግባር ላለው ለሙሽራው
የቀና ሃይማኖት
ደስታው ደስታችን ነውለሙሽራው
ክብሩም ክብራችን ነው
ስነምግባር ላላት ለሙሽሪት
የቀና ሃይማኖት
አጅቧት በደስታ ሙሽሪትን
በሆታ በእልልታ
ስትበቁ ለክብር ለሙሽሮቹ
ለመልካም ትዳር
ጎጆ ስትቀልሱ ለሙሽሮቹ
በእግዚአብሔር ፍቃድ
አብነት ለመሆን የእኛ ሙሽሮች
ለጓደኞቻችሁ
ወልዳችሁ ለመክበድ የእኛ ሙሽሮች
እግዚአብሔር ይርዳችሁ

88. ዕፁብ ነው ድንቅ ነው
<u>ዕፁብ ነው ድንቅ ነው የአምላክ ሥራ</u>
<u>ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሐም ወሣራ</u> /2/
እንዲህ ነው መታደል
በአምላክ መመረጥ
በእግዚአብሐር ቤት መኖር
ከፈተና ማምለጥ
እግዚአብሔር ሲፈቅድ
ሁሉ ይፈፀማል
አሁን እንዳየነው
ጋብቻቸው ደምቋል
ከልብ ያከብራታል
ስለ ሃይማኖቷ
መልካም ስለሆነ
የቀናው ስርዓቷ
አብርሃምን መስሎ
እህቷ ሆይ ሲላት
አቤት ማስቀናቱ
የሙሽሮች ሕይወት
እሷም እንደ ሣራ
ትህትናን ተላብሳ
ጌታዬ ሆይ ብላ
ስሙን ስታነሳ
ያየ ሰው ተደንቋል
በዚህ ሕይወታቸው
በፍቅር ሲኖሩ

እግዚአብሔርን ይዘው

89. የክብሯ መግለጫ
የክብሯ መግለጫ የድንግልናዋ /2/
ይኸው ዛሬ ታየ በተክሊሉ ደምቃ
ይኸው ዛሬ ታየ ካባውን ደርባ
የክብሯ መግለጫ ከሆኑት ነገሮች
" " ቅዱስ ጋብቻ ነው
" " ክብሯን መጠበቋ
" " ከወንድ የመራቋ
" " ተክሊል ተጭኖላት
" " የድንግልናዋ
" " ኮራን በልጃችን
" " በአዲሷ ሙሽራ
የክብሯ መግለጫ ከእናት ከአባቷ ቤት
" " አሸብርቃ ወጣች
" " ረዳት ልትሆነው
" " ወደ ባሏ ሄደች
" " ዛሬስ በዓይናችን
" " ሁላችን አየነው
" " ቀድሞም መኩራታችን
" " ይህንን አውቀን ነው
የክብሯ መግለጫበሥርዓት ማደጓን
" " ዓለም መሰከረ
" " እለል ዘለል ሣትል
" " መኖሯ ታወቀ
" " እንግዲህ ሙሽራው
" " ኩራ ደስ ይበልህ
" " ደግ ጨዋ መርጦ
" " እግዚአብሔር አደለህ

90. እድሜህን ያርዘመው
እድሜህን ያርዝመው እንደ ማቱሳላ
ከትዳር አጋርህ ከሙሽሪት ጋራ/2/
ያርዝመው እንደ ማቱሳላ
ዘመንሽ ይጠቅለል አንቺም እንደ ሣራ
ከትዳር አጋርሽ ከአብርሃም ጋራ/2/
ይጠቅለል አንቺም እንደ ሣራ
የትዳር ጎጆዋችሁ በፍቅር ይሞላ
ልዩነት እንዳይኖር ከእንግዲህ በኃላ /2/
ጎጆዋችሁ በፍቅር ይሞላ

91. ዮም ፍስሓ ኮነ
ዮም ፍስሓ ኮነ
በእንተ መርዓዊ ወመርዓዊሃ
ቆሟል መሠረቱ ------ በእምነት ተመሥርቶ
ብርሃን ይታያል ----- ቤታችውን ሞልቶ
አዝ ............
ተባርኳል ማዕዳችን ----- ጸዋቸውን ሞልቷል

